# የአማራው መከራ ላገሩ ስለሠራ
*(በ ፍቅሬ ቶለሳ ጅግሳ)*

እንሁን ቀና ሰው፣ እውነት እንናገር፣
ለእውነት ጥብቅና፣ ሃቁን አስቀድመን፣
ፖለቲካን ወዲያ፣ ትንሽ አቆይተን፣
እስቲ እንተባበር ሃሰት ላይ አድመን።

እኮ የታለ ፍርድ፣ የታል'ኮ ፍትህ፣
የታለ ባገሩ የሕግ አስከባሪ፣
ኧረ የታል መንግሥት፣
መቅሰፍት የሚሆነው ላገር አሸባሪ?

እንዲህ የሚበድል፣ ማን ነው ውጣ የሚል
ማን ባቀናው ምድር፣ ማንን ከማን ሃገር?
እንዴት የ'ትዮጵያን ልጅ ከ'ትዮጵያ ተነቀል?
ለሰሚ ግራ ነው፣ የሚያሰቅቅ ነገር።

"አማራ" በሚል ሥም
የጠሩት ገበሬ፣
ምን ጥፋት አጠፋ፣
ባዶ አፈር በገፋ በጥማዱ በሬ?
ላቡን እያዘራ ትንፋሹ እስኪያጥር
"ሆ! በሬ" እያለ ካመት ዓመት አርሶ፣
ልጆቹን ባበላ ራሱ ኩርማን ጎርሶ?

ነግዶ በኖረ ላገር ሳይሆን ሸክም፣
ግብር በገበረ ሊጠቅም መንግሥትን፣
በዜግነት ግዳጅ ዋትቶ፣ ወ'ቶ ቢያድር፣
ለምን ይዳረጋል እንዲያጣ እርስትን?
ከ'ባብና ከጊንጥ፣ ከጋሬጣ ታግሎ፣
አሜኬላ ወግቶት፣ ጫካውን መንጥሮ፣
ያለማውን መሬት ለምን ይነጠቃል?
ያፈራውን ቅሪት ግሮ ተጣጥሮ?

ባዕድ ሃገር ሄዶ ሰው ሲኖር አልፎለት፣
የሰብአዊ መብቱ ንብረቱም ተከብሮ፣
እንዴት ሰው ካገሩ በግፍ ይነቀላል?
እንዴት ዐውድ ይጣላል ከነልጆቹ አብሮ?

ምን ዐይነት ጭካኔ የፍርድ መረገጥ፣
ምንድን ዐይነት ግፍ ነው፣
ምንድን ፍትህ እጦት፣
ምን ሕግ-አልባነት ነው እንዲህ የገነነው?

ከባሕሩ ማዶ መጣ 'ንዴ አማራ፣
አልተፈጠረም ወይ በኢትዮጵያ ምድር፣
ምን የቆረጠው ነው በገዛ ሃገሩ፣
የሚከለከለው ባሻው እንዳያድር?

የማራ ልጅ ነኮ ጎጃም የበቀለ፣
አጎቱ መደባይ የኦሮሞ አባት፣
የሁል አባት ደሸት፣ ፈላስፋው ነቢዩ፣
የኢትዮጵ ዘር ያምላክ፣ የተቀባ ቅባት።

የእራስ ላጭን ልጅ አሉ ተባይ በላው፣
የአባይንም ልጅ አሉ ውሃ ጠማው፣
የግንበኛውን ልጅ ቤት አጥቶ ጅብ በላው፣
የዘበኛውን ልጅ ወንበዴ 'ኮ ቀማው!

ምን ትላለህ ደሸት፣ ምን ትላለህ ማራ፣
ልጅህ አይኑር ሲባል ባቀናኸው መሬት፣
ምን ልትል ኢትዮጵ ባለማኸው ምድር፣
ዘርህ መድረሻ አጥቶ፣ ሲያነባ በምሬት?

ማራማ ያንተ ልጅ በጥንት በጠዋቱ፣
"አማራ" ተብሎ ወደር-የለሽ ጎበዝ፣
ኖረ አገር ሲያቀና ድንበሩን ሲያስከብር፣
ለራሱ መርጊያ አጥቶ፣ ላገር ሲቅበዘበዝ።

ጸጥታ እዲያስከብር፣ ቀዳማይ ምኒልክ
ሰሜን፣ ደቡብ፣ ምሥራቅ፣ እዛ 'ዚ ሲልከው፣
በ'ትዮጵያ ዳር ድንበር፣ ካፍሪካም ባሻገር፣
ትንፋሽ አስቆርጦ ሲአስለከልከው፣

የልጁ ልጅ ዘግዱር የአክሱማይ አባት፣
አክሱም ፈርዓኦን ሆኖ መንግሥቱ እንዲጠና፣
በግብጽ አሰማርቶት ሲጠብቅ ዙፋኑን፣
የማራ ልጅ አቅም መች ተሟጠጠና፣
እንግልቱ፣ ክልውሱ መቼ አበቃና፣
ንጉሥ ነገሥት ሆኖ አክሱማይም አድጎ፣
ልጁን ራብላን ሲድር፣ ለኢራኩ ንጉሥ ለናቡከድነፆር፣
ያ ምስኪን አማራ እንደገና ታጥቆ፣ ፈለሰ አደግድጎ።

ፍለሳው ግን ከንቱ አልቀረም ላማራ፣
ለድካሙ ዋጋ ለሥም መታሰቢያ፣
"አማራ" የሚሰኝ በኢራክ አሁን ያለ
ከተማ ከተመ ታዲያ በዚያ ሳቢያ።

ላሊበል ሲመለስ ከሳሌም ስደቱ፣
በግብጽ አለፈና ሄዶ ካማራው ዘንድ፣
አማራው በምሥር ሺ ስምንት መቶ ዓመት
ከኖረ በኋላ፣ ወስዶት ያማራን ወንድ፣
በኢትዮጵያ ምድር ተዋግቶ አነገሠው፣
ላሊበል አማራን ሾሞት በመንግሥቱ፣
ቋንቋውን አረገው ብሄራዊ ቋንቋ፣
ወታደር አረገው አስፍሮ በርስቱ።

ቋንቋው ተወዶለት በንጉሥ፣ በወታደር፣
የቅኔው ውበቱ፣ የሰምና ወርቁ፣
ላእምሮ ጅምናስቲክ፣ ለልብ ምርምር፣
ቃላቱ ምሥጢሮች ነፍስን የሚሰርቁ።

ግን የቋንቋው ውበት፣ ላማራው አልበጀው--
ለጉረሮ እሚመች እማያስቸግረው፣
ለምላስ፣ ለከንፍር ቢሆን እሚስማማው፣
ገዢ መስሎ ታየ ሁሉም ቢናገረው።

የዛግዌ ንጉሥ ዘር ኋላም ቢያፈርስ ቃል፣
ይኩኖ-ዓምላክም አምኖ ቢለምነው፣
ከምኒልክ አልጋ አስቀምጠኝ ቢለው፣
ተዋግቶ አነገሠው ታምኖ ለእሚያምነው።

የ'ሥራኤል ዝርዮች እኒያ አጋዝያኑ፣
ሲያስጠብቁት ኖረው ዙፋንና ጠረፍ፣
ወራሪም ሲመጣ እግሮቹን ለጠጠር፣
ደረት ለጦር ዳርጎ ከቶም ያለማረፍ፣
ዛጉዌና አጋዝያን ሁሌም ነግሠው ሳሉ፣
ሲባል ተወራበት "አማራው ነገሠ"፣
ቋንቋው ብሄራዊ በመሆኑ ብቻ፣
ሌሎች እንዲበሉ እሱ በደገሰ።
ባልዋለበት ቦታ ብለውት ውለሃል፣
መሳፍንት በበሉት በልተሃል ብለውት፣
ነገሥታት ባረጉት ብለውት አርገሃል፣
ያማራን ሰራዊት ጎዱት በድለውት።
እሱን ማስፈራሪያ፣ ጭራቅ አውሬ አርገውት፣
ሥንቶቹ ጉብ! አሉ ከሥልጣን ኮርቻ፣
እንደአሸን ፈልቀው ከበላዩ ውለው፣
እሱን ጨፈላልቀው ጥለው ከሥርቻ።

ታዲያ ኢትዮጵያና መንግሥቷ እንዲቆሙ፣
ደሙን እያዘራ በተከሰከሰ፣
ያላግባብ ተከሶ፣ ካቀናው ሃገር ላይ
ተነቅሎ ተጣለ፣ ከውሻ ረከሠ።

ደሙ ግን ይጮሃል ልክ እንደ አቤል ደም፣
ግን በምድር ካጣ፣ ፈራጅ ወይ ተበቃይ፣
እንዲህ ከመረረው ግፉ ወሰን አልፎ፣
ሠይፍም መምዘዝ ያውቃል ከባሰበት ስቃይ።

ጻሩ ዘር ተቆጥሮ ይውጣ ከተባለ፣
አማራውን ብቻ ለምንድነው ታዲያ?
ይመለስ ጉራጌ፣ ይሂድ ከጉራዕጌ፣
ወለጋው ወለጋ፣ ሃዲያው ሃዲያ፣
የትግራዩ ትግራይ፣ ሲዳሜው ሲዳሞ፣
የሃረሩ ሃረር ተባሮ ይውጣና፣ ታዲያ ከዛ ወዲያ

ሺ አገር ተፈልፍሎ፣ እንዲሁም ሺ መንግሥት፣
ሁሉም በየፊናው ሆኖ ያገር መሪ፣ መንግሥት
ሆኖ በሽበሽ፣ የመሪው ቁጥሩ በዝቶ ከተመሪ፣
የባቢሎን ቋንቆች ሰፍነው በዚህ ማግስት፣
የመግባቢያ ቋንቋ ጠፍቶ አብሮ ንግዱ፣
የደቦ እርሻ ቀርቶ መካፈሉም እርስት፣
የራስን ምርት ለራስ ተስገብግቦ ይዞ፣
በባይታወርነት እየኖሩ ለራስ፣ ሁሉ ለራስ ብቻ፣
ሁሉ ዐይነት ተሳስሮን፣ ብጥስ-ጥስ-ጥስ አርጎ፣
ይቅራ መዛመዱ፣ ባምቻ በጋብቻ::

በቃ አዲስአበባም፣ "ፊንፊኔ ነኝ" ብላ፣
ሸዌ ያልሆነውን፣ አባርራ አስወጥታ፣
ቤት ንብረት ሕንፃውን፣ ገንዘቡንም ነጥቃ፣
ሜዳ ታፍስሰዋ፣ ሁሉን አሳጥታ!

ሁሉም ድንበር አጥሮ፣ የቤርሊን ቻይና ግንብ፣
የእግር ቦምብ ቀብሮ፣ ደማሚት ሾህ ሽቦ፣
ደሜትን ይሁና ሁሉም ተከርችሞ፣
ተስቦ እንደያዘው ርቆ ተወሽቦ::

ዛሬ አማራ ሆኖ ነገ ሌላው ጭዳ፣
በሰፈሩት ቁና፣ አይቀር መሰፈሩ፣
ኪብሪት የለኮሰ ሲዛመት እሳቱ
አይተርፍም ከመንደድ፣ ጭራሽ ከመንፈሩ::

እህል ከብቱን ነጥቆ፣ ላቡን ገንዝብ ዘርፎ፣
ቤቱን አፈራርሶ፣ ደግኖ አፈሙዝ፣
ማነው አማራውን የጣለው መንገድ ላይ፣
እውነት ኦሮሞ ነው፣ ሺናሻ ወይ ጉሙዝ?

ሃቁ ፍንትው ብሎ፣ ይታይ ተገላልጦ፣
ያማራ አጎቱ፣ የመደባይ ልጁ፣ እውነት
ጨክኖበት ኦሮሞ ዘመዱ፣
ከመሬት ነቀለው በአረመኔነት?
ኦሮሞማ ገር ነው የነቢይ ደሸት ልጅ፣
ሺናሻም የዋህ ነው፣ ደግ ነው ጉሙዝም፣
ግን አለ መሰሪ ያደባ በጀርባ፣
ዘመዳም እሚያፋጅ፣ ዕድሜው እንዲረዝም::

የፍርድ ቀን ሲደርስ፣ እውነቱ ተገልጦ
በሸለቆ ባምባው የተሰራጨ እለት፣
ወዮ! እሱን አያርገኝ! "ባክሽ ምድር ዋጭኝ!
"ዋ! ባልተፈጠርኩኝ!" በሚል ወቅት ወዮለት!

እአአ 3/29/2013

ለዚህ ግጥም ደራሲ የሚሰማዎትን አስተያየት ለመስጠት ከአሻዎት በሚከተለው ኢሜል አድራሻ ይገናኙት:: -- *ftolossa@aol.com*